

# የአዲስ ታካሚ ውሂብን መሰብሰብ

## በቀጣይ ጊዜ ወደ ሆስፒታል ሲሄዱ፣ ስለ ዘር፣ ብሔር፣ ቋንቋ፣ ወሲባዊ ዝንባሌ፣ ጾታ እና አካል ጉዳት አዳዲስ ጥያቄዎችን ሊመለከቱ ወይም ሊጠየቁ ይችላሉ።

ሆስፒታሎች ስለ ታካሚ ቆይታ ለ Washington State Department of Health (DOH፣ የዋሺግተን ግዛት የጤና መምሪያ) መረጃዎችን ያጋራሉ። በአሁኑ ጊዜ የሆስፒታል የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች ታካሚዎችን ስለ ዘር፣ ብሔር፣ ቋንቋ፣ ወሲባዊ ዝንባሌ፣ ጾታ እና አካል ጉዳት መረጃ እንዲጠይቁ የዋሺንግተን ህግ ይጠይቃል።

DOH አዲሶቹን ምድቦች በሚያዘጋጅበት ጊዜ ከዋሺንግተን ማህበረሰቦች ጋር ሰርቷል። ይህ መረጃ ግዛቱ የሆስፒታል አገልግሎቶችን ማን እንደሚጠቀም እና ለምን ምክንያቶች እንደሚጠቀም እንዲረዳ ያግዘዋል። DOH ማህበረሰቦች ሆስፒታሉን እንዴት እንደሚጠቀሙ በሚረዳበት ጊዜ፣ ማህበረሰቦቹን በደንብ ትርጉም በሚሰጥ መንገድ ልናገለግላቸው እንችላለን።

## ለምን እንጠይቃለን

ለእነዚህ ጥያቄዎች የሚሰጡት መልስ የህብረተሰብ ጤናን ይረዳል። የህብረተሰብ ጤና ባለስልጣናት በጤና እንክብካቤ ተደራሽነት፣ በጤና እንክብካቤ እኩልነት፣ እና በጤና ውጤቶች አለመመጣጠኖች ማን በጣም እንደተጎዳ ማወቅ ይፈልጋሉ። ማህበረሰቦች ሆስፒታሉን እንዴት እንደሚጠቀሙ በምናውቅበት ጊዜ፣ ማህበረሰቦቹን እንዴት በደንብ መርዳት እንደምንችል ማቀድ እንችላለን። የጤና እንክባክቤ አለመመጣጠኖች ውስብስብ ናቸው። የበለጠ በተረዳን ቁጥር የተሻለ መሆን እንችላለን።

## ውሳኔው የእርስዎ ነው

እነዚህን ጥያቄዎች መመለስ ወይም አለመመለስዎ የእርስዎ ምርጫ ነው። ሆስፒታሉ ሁሉንም ጥያቄዎች እርስዎን መጠየቅ ያለበት ቢሆንም፣ መልስ እንዲሰጡ አይገደዱም። መልስ መስጠት ለማይፈልጓቸው ጥያቄዎች፣ "Patient declined to respond (ታካሚው መመለስ አይፈልግም)" የሚለውን መምረጥ ይችላሉ። DOH እነዚህን ሁሉንም ጥያቄዎች ይመልሳሉ ብሎ ተስፋ ያደርጋል፣ ስለዚህም እርስዎን እንዲሁም ሁሉንም የዋሺንግተን ነዋሪዎች በተሻለ ሁኔታ ማገልገል እንችላለን።

## ግላዊነቴን እንዴት ትጠብቃላችሁ?

ሁሉም ሰው እነዚህን ጥያቄዎች በመመለሱ ደህንነት እንዲሰማው እንፈልጋለን። መረጃዎ በጥብቅ ምስጢራዊ ነው እንዲሁም እንደ ምስጢራዊ የህብረተሰብ ጤና መረጃ ይታሰባል። DOH መረጃዎን ሪፖርት ሲያደርጉ እንደ ስም ወይም የልደት ቀን የመሳሰሉ ግላዊ መረጃዎችን አያካትትም።

መረጃዎን ለእኛ በማጋራት፣ SNAP ወይም Apple Health የመሳሰሉ፣ ከግዛት የሚያገኟቸው ማንኛውም ጥቅማ ጥቅሞች ላይ ተፅዕኖ አይኖረውም። ይህ መረጃ ለኢሚግሬሽን ባለስልጣናት አይጋራም።

Washington State Department of Health

ይህን ሰነድ በሌላ ቅርጸት ለማግኘት፣ ወደ 1-800-525-0127 ይደውሉ። መስማት የተሳናቸው ወይም መስማት የሚቸግራቸው ደንበኞች ወደ 711 (Washington Relay) መደወል ወይም ወደ civil.rights@doh.wa.gov ኢሜይል ማድረግ ይችላሉ።

DOH 422-237 December 2022 Amharic